pdf by @shuktus_books




Scanned by DocumentScanner | Lufick

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

© ALL RIGHT RESERVED

አከፋፋይ፦ አዮብ መጻሕፍት መደብር

+251-929-46-82-82

+251-909-52-52-83

ስለ መጽሐፉ አስተያየትና ጥያቄዎች ካለዎት

wooddeg@gmail.com





## ለደራሲው የተሰጡ አስተያየቶች

**የተከበሩ ዶ/ር ሂል፡-**

እሁን የስኬት ሕግ መጽሐፍትዎን አንብቤ ለመጨረስ ስለቻልኩ ይህን ፍልስፍና በማዘጋጀት ስለአደረጉት አስደናቂ ሥራ አድናቆቴን ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡ ትምህርትዎ የተመሰረተባቸውን አሥራ ሰባት መርሆች የሀገሪቱ እያንዳንዱ ፖለቲከኛ ቢያውቃቸውና ቢተገብራቸው ጠቃሚ ይሆናል፡፡ መጽሐፍዎ በየትኛውም የህይወት ዘርፍ ላለ ማንኛውም መሪ ማወቅ ያለበትን እጅግ ጠቃሚ መረጃ ይዟል፡፡ በዚህ አስደናቂ የተፈጥሮ "እውቀት ፍልስፍና" ትምህርት ዝግጅትዎ ወቅት የተወሰነ ድጋፍ ለማድረግ ዕድሉን በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ፡፡

የእርስዎ

(ፍራንክሊን ሩዝቬልት የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት እና ጠቅላይ ፍ/ቤት ዋና ዳኛ)

**የ5 ዶላር ከ10 ሳንቲም መደብሮች ንጉሥ፡-**

የስኬት ሕግ ፍልስፍናን አስራ ሰባቱን መርሆች ብዙዎችን በመተግበር እጅግ በርካታ ውጤታማ መደብሮችን ለመስራት ችለናል፡፡ የውልወርዝ ሕንፃ የእነዚህ መርሆች የትክክለኝነት መገለጫ ህውልት መሆኑ ስናገር እውነት አጋኖ ማቅረብ እንዳልሆነ እምናለሁ፡፡



Scanned by DocumentScanner | Lufick

በትንሽ ትምህርት፣ ያለ ምንም ገንዘብ፣ ያለ ተፅዕኖ ፈጣሪ ጓደኞች ወደ ከፍተኛ ቦታ ስለ ወጣበት ዘዴ የሰጡት እስደናቂ ገለፃ ትናት እንደሆነ ያህል እስታውሰዋለሁ፡፡ ንግግርዎን ከመጨረስዎ በፊት፥ ምንም ያህል ችግሮች ቢገጥሙኝ ለራሴ ቦታ ለመስጠት አእምሮዩን አዘጋጀሁ፡፡

በሺህዎች የሚቆጠሩ ልጆች በዚህ አመት እና በቀጣይ ጥቂት አመታት ትምህርታቸውን ይጨርሳሉ፡፡ እያንዳንዳቸው እኔ ከእርስዎ እንደአገኘሁት ያለ ተግባራዊ የማበረታቻ መልዕክት ይፈልጋሉ፡፡ ወዴት መታጠፍ፥ ምን ማድረግ፥ ህይወትን እንዴት መጀመር እንዳለባቸው ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡ የብዙ ብዙ ሰዎን ችግር በመፍታት ስለረዱቸው ሊነግሯቸው ይችላሉ፡፡ ሀሳቦችን እንዴት ወደ ገንዘብ መቀየር እንደሚችሉ ማወቅ የሚፈልጉ፣ በትንሽ ወይም ያለ ምንም ገንዘብ መጀመር ያለባቸው እና ከውድቀቶቻቸው መነሳት ያለባቸው ሰዎች ዛሬ በአሜሪካ ሺህዎች ናቸው፡፡ የሚረዳቸው ሰው ካለ፥ እርስዎ ነዎት፡፡

መጽሐፉን ከአሳተሙ የእርስዎ የግል ማስታወሻ የተፃፈበት ከማተሚያ ቤት የወጣ የመጀመሪያው ኮፒ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡፡

*መልካሙን ሁሉ የምመኝሎት የእርስዎ ናፋቂ*

*ጀኒንግስ ራንዶልፍ*

ያን ንግግር ከአደረግሁ ከሠላሳ አምስት ዓመት በኃላ፥ በ1957 ወደ ሳሌም ኮሌጅ ተመልሼ የምርቃ በዓል ላይ ሰብከት ማድረግ ደስታዬ ነበር፡፡ ያን ጊዜ ከሳሌም ኮሌጅ በስነ-ጽሁፍ የክብር ዶክትሬት አገኘሁ፡፡

ከ1922 ጀምሮ፥ ጀኒንግስ ራንደልፍ ከሀገሪቱ ዋና የአየር መንገድ ባለስልጣናት አንዱ ለመሆን ሲበቃ፣ ትልቅ ተናጋሪ እና ከምዕራብ ቨርጂንያ የተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች ሴናተር ሲሆን አይቻለሁ፡፡





## የሰዉ አዕምሮ የሚያስበዉን የሚያምነዉን ማንኛዉም ነገር ያሳካለ፡፡



Scanned by DocumentScanner | Lufick

**ከምንቀበላቸዉ በቀር የአዕምሮ ገደቦች የሉም፡፡**

**ድህነትና ሀብት የሀሳብ ልጆች ናቸዉ፡፡**





## III

## እምነት

## ፍላጎትን በዓይነ-ህሊና ማየት እና በማግኘት ማመን

## *ወደ ሀብቶች ሁለተኛው እርምጃ*

እምነት የአዕምሮ ዋና ኬሚስት ነው፡፡ እምነት ከሀሳብ ጋር ሲደመር÷ ልክ እንደ ፀሎት÷ በቅፅበት ድብቁ አእምሮ ምገዱን ይቀበላልና ወደ መንፈሳዊ ተመጣጠኙ ይቀይረዋል፤ ከዚያም ወደ ሁለንተና ጥበብ ያስተላልፈዋል፡፡ የእምነት፣ የፍቅር እና የወሲብ ስሜቶች ከሁሉም ዋና እምንታዊ ስሜቶች እጅግ ሃይለኞች ናቸው፡፡ ሶስቱ ሲጣመሩ÷ ሁለንተና ጥበብ መልስ እንዲሰጥ የማድረጊያ ብቸኛ መንገድ ናቸው፡፡ እምነት ወደ መንፈሳዊ ተመጣጣኙ ወደሚቀየርበት ወደ ድብቁ አእምሮ በቅፅበት እንዲደርስ በማድረግ ሀሳብን "የማስዋብ" ውጤት አላቸው፡፡

### እምነትን ማሳደግ

እነሆ÷ ስለ ግለ-አስተያየት የተሻለ አረዳድ የሚሰጥ÷ ፍላጎትን ወደ አካላዊ ወይም ገንዘባዊ ተመጣጣኙ መቀየር የሚያስችል አባባል አለ፡፡ እሱም፡- እምነት በግለ አስተያየት መርሀ÷ ሀሳቦችን ለራስ ደጋግሞ በመንገር ወይም ድግግሞሻዊ ትዕዛዞችን ወደ ድብቀ አእምሮ በመላክ የሚመጣ ወይም የሚፈጠር የአእምሮ ገፅታ ነው የሚል ነው፡፡



Scanned by DocumentScanner | Lufick

ሀሳቦች የማይጨበጡ ሃይሎች ናቸው፡፡ ከወለዳቸው አካላዊ አእምሮ እጅግ የሚበልጥ ኃይል አላቸው፡፡ የፈጠራቸው አእምሮ ወደ አፈር ከተመለሰም በኋላ የመናገር ሃይል አላቸው፡፡





VII

## የተደራጀ ዕቅድ

## ፍላጎትን ወደ ተግባር የመጠንከር ሂደት

## *ወደ ሀብቶች ስድስተኛው እርምጃ*

የሰው ልጅ የሚፈጥረው ወይም የሚያገኘው ማንኛውም ነገር በፍላጎት መልክ እንደሚጀምር እና የፍላጎት ጉዞ የመጀመሪያ ክፍል ከረቂቅ ወደ ተጨባጭ ለመለወጥ ዕቅዶች በሚፈጠሩበት ወይም በሚደራጁበት ወደ ምናብ መስሪያ ክፍል እንደሚወሰድ ተምረሃል፡፡ በምዕራፍ ሁለት፥ የገንዘብ ፍላጎትን ወደ ገንዘባዊ ተመጣጣኙ በመቀየር እንደ መጀመሪያ እንቅስቃሴህ ስድስት ውሱን፣ ተግባራዊ ደረጃዎችን እንድትተገብር ታዝዘሃል፡፡ ከእነዚህ ደረጃዎች አንዱ ይህ ለውጥ የሚደረግበት ውሱን ተግባራዊ ዕቅድ ወይም ዕቅዶች ማዘጋጀት ነው፡፡ አሁን ተግባራዊ የሚሆኑ ዕቅዶችን እንዴት እንደምትገነባ ትማራለህ፡፡ እነርሱም፡-

ሀ) ገንዘብ የማግኘት ዕቅድህን ወይም ዕቅዶችህን ለመፍጠር እና ለመተግበር በሚመጣው ምዕራፍ የተገለጠውን "የላዕላይ አእምሮ" መርህ በመጠቀም ከሚያስፈልግህ ያህል ብዙ ሰው ጋር ተባበር፡፡ (ለዚህ መመሪያ መታዘዝ ሙሉ በሙሉ አስፈላጊ ነው፡፡ አትተወው፡፡)

ለ) "የላዕላይ አእምሮ" ህብረት ከመፍጠርህ በፊት፥ ለቡድንህ አባላት ስለትብብራቸው የምትሰጣቸውን ቦታ እና ጥቅሞች ወስን፡፡ ያለ ምንም ክፍያ ማንም ያለ ገደብ አይሰራም፡፡ ብልህ ሰው ያለ በቂ ክፍያ እንዲሰራ ሌላ ሰው አይጠይቅም ወይም አይጠብቅም_ ምንም እንኳ ይህ ሁሌግዜ በገንዘብ መልክ ባይሆንም፡፡



Scanned by DocumentScanner | Lufick

ደስታ በማግኘት ብቻ ሳይሆን
በመሥራት ይገኛል፡፡





## XI

## __የወሲብ ቅየራ ጥበብ__

### ሃይልን በአግባቡ የመጠቀም ጥበብ

### ወደ ሀብቶች አስረኛው እርምጃ

"ቀየረ" የሚለው ቃል በቀላል አነጋገር "አንድን ነገር ወይም አንድን የሃይል አይነት ወደ ሌላ መለወጥ ወይም ማስተላለፍ" ማለት ነው፡፡ የወሲብ ስሜት የአእምሮ ገፅታ ይሆናል፡፡ ባለማወቅ፤ ይህ የአእምሮ ገፅታ ከጠቅላላ አካላዊ ከፍሎች ጋር ይገናኛል፡፡ እንዲሁም ተገቢ ባልሆኑ ተፅዕኖዎች፤ ብዙ ሰዎች ስለ ወሲብ ያላቸውን እውቀት የሚያገኙበት በመሰረቱ አካላዊ ነገሮች በመሆናቸው፥ በሃይለኛው አእምሮን ገድበውታል፡፡

የወሲብ ስሜት ከበስተጀርባው ሶስት ተገቢ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ እነርሱም፡-

1. የወሲብ ዘርን ለመተካት
2. ጤንነትን ለመጠበቅ (እንደ እሱ የሚሆን መድሃኒት የለም)
3. በቅየራ ስንፍናን ወደ ልዩ እውቀት ለመለወጥ

የወሲብ ቅየራ ቀላል እና በግልፅ የሚገባ ነው፡፡ እሱም አካላዊ መገለጥ ከሆኑ ሀሳቦች ወደ ሌላኛ አይነት ሀሳቦች ወደ ማሰብ አእምሮን መቀየር ነው፡፡



Scanned by DocumentScanner | Lufick

### የውጤታማ ጸሎት ምስጢር

አስተዋይ ሰው ከሆንክ ፥ ብዙ ሰዎች ሁሉም ነገር ካለፈ በኋላ ጸሎት ሲያደርጉ ታያለህ፡፡ ወይም በተለመዱ ትርጉም አልባ ቃላት ይፀልያሉ፡፡ እናም ሁሉም ካለፈ በኋላ ስለሚፀልዩ ብዙ ሰዎች አእምሮአቸው በፍርሃት እና በጥርጣሬ ተሞልቶ ለጸሎት ይነሳሉ፡፡ ድብቁ አእምሮም የሚቀበላቸው እና ወደ ሁለንተና ጥበብ የሚያስተላልፋቸው እነዚሆን ስሜቶች ነው፡፡ አንድ ነገር ከአላመንክ ÷ ነገር ግን ስትፀልይ እንደማታገኘው ወይም ጸሎትህ ወደ ሁለንተና ጥበብ እንደማይደርስ ከፈራህ ጸሎትህ ከንቱ ነው፡፡ ጸሎት አንዳንዴ የፀለይከው ነገር እውን እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ፀሎት አድርገህ መልስ ያገኘህበት ወቅት ካለ÷ ወደ ትውስታህ ተመለስና ስትፀልይ በነበረበት ወቅት የነበረህን ትክክለኛ ልቡና አስታውስ፡፡ እናም በእርግጠኝነት እዚህ ላይ የተገለጠው ቴዎሪ ከቴዎሪ በላይ እንደሆነ ታውቃለህ፡፡ ከሁለንተና ጥበብ ጋር የምትገናኝበት ዘዴ ሬድዮ የድምፅ ሞገዶችን ከሚቀበልበት መንገድ ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው፡፡ ሬድዮን የሚሰራበትን መርህ ከአወቅህ÷ እዎ ታውቃለህ÷ የሰው ጆሮ እስከሚሰማበት የሞገድ ፍጥነት እስኪቀየር ድረስ ድምፅ እንደማይሰማ ታውቃለህ፡፡ ሬድዮ ማስተላለፊያ ጣቢያ የሰውን ድምፅ ተቀብሎ ሚሊዮኖች ጊዜ ምገዱን በማሳደግ ያስተካክለዋል፡፡ በዚህ መንገድ ብቻ ነው የድምፅ ጉልበት በህዋ ላይ መልእክት የሚያስተላልፈው፡፡ ይህ ለውጥ ከተከናወነ በኋላ መልዕክቱ (በመጀመሪያ በድምፅ ሞገዶች መልክ የነበረ) ከሬድዮ መቀበያዎች ይደርስና ድምፅ ሆኖ እንዲሰማ እነዚህ መቀበያዎች እንደገና ወደ መጀመሪያው የሞገድ ፍጥነት ይቀይሩታል፡፡ ድብቁ አእምሮ ጸሎቶችህን ወደ ሁለንተና ጥበብ በማስተላለፍ መልእክቱን አድርሶ የፀሎቱን አላማ ለመስጠት መልሱን በተወሰነ ዕቅድ ወይም የሀሳብ መልክ የሚያመጣ መካከለኛ ነው፡፡ ይህን መርህ ተረዳ፡፡ እናም ቃላትን ብቻ ከጸሎት መጽሐፍ ማንበብ በሰው ልጅ አእምሮ እና በሁለንተና ጥበብ መካከለኛ ሊሆን አይችልም፤ አይሆንምም፡፡





ማንኛዉም ሰዉ ሀብት ይመኛል። በጣም ጥቂቶች ግን ፤ ዉስን እቅድ እና ከፍተኛ ፍላጎት ሀብት የማግኛ መንገድ እንደሆነ ያዉቃሉ።



Scanned by DocumentScanner | Lufick

ተመሳሳይ ዕቅድ በማውጣትና በመተግበር የዚህ ፍልስፍና ማንኛውም ጠቀሜታ በመግቢያው ላይ በአጭሩ የተገለጠውን አስደናቂውን የካርነጊ ቁመር የራሱ ያደርጋል፡፡ አሁን ምንም ከአልመሰለህ÷ ይህን ገፅ ምልክት አድርግበት እና የመጨረሻውን ምዕራፍ ከጨረስክ በኋላ እንደገና አንብበው፡፡





የስኬት መሠላል ጫፉ ላይ አይጠብም፡፡



Scanned by DocumentScanner | Lufick

## ስለ ደራሲው

ዶ/ር ናፖሊዮን ሂል ዝነኛና ታዋቂ ደራሲ፣ ጋዜጠኛ፣ ስራ ፈጣሪ፣ ጠበቃ እና መምህር ነው፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ በመቶ የሚቆጠሩ እጅግ ስኬታማ ሰዎችን ሲያተጠና ኖሯል፡፡ ከእነሱም አንድሪው ካርነጊ፣ ቶማስ ኤድሰን፣ አሌክሳንደር ግርሃም ቤል፣ ሉተር ቡርባንክ፣ ሄነሪ ፎርድ እና ቻርለስ ሸዋብ ይገኙበት፡፡ ለሁለት አሜሪካ ፕሬዝዳንቶች ለውድሮው ዊልሰን እና ለፍራንክሊን ሩዝቬልት አማካሪ ነበር፡፡ በመጽሐፍቶቹ እና በትምህርቱ ለአሜሪካ ሕዝብ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ለብዙ ሚሊዮን ሰዎች ባለውለታቸው ሆኗል፡፡ በሰው ልጅ የስኬት ሳይንስ እና ፍልስፍና ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ Think and Grow Rich, You Can Work Your Own Miracles, The Master-Key to Riches, With Peace of Mind, Success Through a Positive Mental Atitude, Outwitting the Devil,........የተሰኙ በርካታ የስኬት እና ራስን የማሻሻል መጽሐፍትን ጽፏል፡፡

pdf by @shuktus_books